# እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው?
# Qui sont ces personnes?







ዐፄ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ

L'empereur Ménélik et l'impératrice Taytu

Impératrice d'Éthiopie de 1869 à 1913.

# አፍሪካን መከፋፈል
# La ruée vers l'Afrique




በ1877 ዓ.ም. የአውሮፓ መንግሥታት “የበርሊን ኮንፈረንስ” በተባለው ስብሰባ አፍሪካን ተከፋፍለው በጦርነት ለመያዝና ቅኝ ለመግዛት ተስማሙ።

En 1884, les puissances européennes se sont réunies à l'occasion de la «Conférence de Berlin» et ont convenu de se partager l'Afrique et de la coloniser.

# ቅኝ ግዛት
# La colonisation

ከኢትዮጵያ በስተቀር ሙሉውን አፍሪካ በቅኝ ግዛት ያዙት። ኢትዮጵያ ብቻ ነፃ አገር ነበረች።

Les Européens ont colonisé toute l'Afrique, à l'exception de l'Éthiopie. Seule l'Éthiopie était un pays indépendant.



# የጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረር መፈለግ
# La volonté de l'Italie de conquérir l'Éthiopie




ብዙ የቅኝ ግዛት አገር ያልነበራት ጣልያን ብቸኛዋን ነፃ አገር ኢትዮጵያ ለመያዝ ፈለገች።

L'Italie, qui ne possédait pas beaucoup de terres coloniales, voulait conquérir l'Éthiopie, le seul pays indépendant.



# የውጫሌ ውል
# Le traité de Wuchale

ኢትዮጵያና ጣልያን በጋራ ለመሥራት የውጫሌ ውል የሚባል የትብብር ውል ተዋዋሉ። የአማርኛው ውል በትክክል ሲጻፍ ጣልያን ግን በጣልያንኛው ላይ ኢትዮጵያ በጣልያን ቅኝ ግዛት ሥር እንዳለች የሚያስመስል ሀሳብ ጨመረችበት።

L'Éthiopie et l'Italie ont signé le Traité de Wouchalé. Alors que la version amharique était écrite correctement, l'Italie a ajouté une idée à la version italienne qui prétendait que l'Éthiopie



Article 17 of the Wuchale Treaty

# የውጫሌ ውል
# Le traité de Wuchale

ዐፄ ምኒልክ ጣልያን ውሉን እንድታስተካክል በተደጋጋሚ ቢሞክሩም ጣልያን ጦርነት እናደርጋለን ብላ ዛተች።

L'empereur Ménélik tente à plusieurs reprises de persuader l'Italie de modifier le traité, mais l'Italie menace d'entrer en guerre.



# አዋጅ

# Proclamation



ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ። እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ፡፡ እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉም ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም፡፡ ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም፡፡

አሁንም አገር የሚያጠፉ ሃይማኖት የሚለውጥ እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል፡፡ እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር።

አሁን ግን፡ በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም፡፡ ያገሬ ሰው ከአሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም፡፡ አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም፡፡ ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበትም የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በሀዘንህ እርዳኝ፡፡ ወስልተህ የቀረህ ግን፡ ኋላ ትጣላኛለህ፡፡ አልተውህም። ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ።

## ስለዚህ ዐፄ ምኒልክ የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን ከጠላት እንዲከላከል ለጦርነት እንዲዘጋጅ አዋጅ አወጁ።

## Ainsi, l'empereur Ménélik a proclamé que le peuple éthiopien devait se préparer à la guerre pour défendre son pays contre l'ennemi.

# የኢትዮጵያና የጣልያን ወታደሮች
# Les soldats éthiopiens et italiens



በኢትዮጵያና በጣልያን ወታደሮች መካከል ምን ምን ልዩነቶች ይታዩአችኋል?

Quelle différence voyez-vous entre les soldats éthiopiens et italiens?



# የኢትዮጵያ ወታደሮች
# Les soldats éthiopiens

ጥሩ የወታደር ልብስ፣ ጫማ፣ ኮፍያ
የላቸውም።
ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የላቸውም።
ዘመናዊ የጦርነት ሥልጠና የላቸውም።
ከሩቅ ቦታ በእግሩ ለብዙ ወራት ተጉዘዋል።

Ils n'avaient pas de bons vêtements militaires, de chaussures, de chapeaux.

ils n'avaient pas d'armes modernes

ils n'ont pas reçu d'entraînement à la guerre moderne.

Ils ont voyagé à pied pendant plusieurs mois à partir d'un endroit éloigné

# የጣልያን ወታደሮች
# Les soldats italiens

ለውጊያ የሚመች የወታደር ልብስ፣ ጫማ፣
ኮፍያ አላቸው።
ዘመናዊ የጦር መሣሪያ አላቸው።
ምግብና መጠጥ በደንብ ይቀርብላቸዋል።
ዘመናዊ የጦርነት ሥልጠና ወስደዋል።

Ils avaient des vêtements, des chaussures et des chapeaux militaires adaptés au combat.

Ils disposaient d'armes modernes.

La nourriture et les boissons sont bien servies.

Ils ont reçu un entraînement à la guerre moderne

# የኢትዮጵያ ወታደሮች
# Les soldats éthiopiens

# የጣልያን ወታደሮች
# Les soldats italiens

የዘመቱት አገራቸውን ከወራሪ ለመከላከል፣ ጠላትን ለማሸነፍና ለእኛ ነፃ አገር ለማስረከብ ነው።

Ils ont marché pour défendre leur pays contre les envahisseurs, vaincre l'ennemi et nous transmettre un pays libre.



የዘመቱት የሰው አገር ለመውረርና ለመቀማት ነበር።

Ils ont défilé pour conquérir et occuper la terre qui n'est pas la leur.



# ጦርነት
# La guerre

- አምባ አላጌ

  Amba Alage

- መቀሌ

  Mekele

- ዓድዋ

  Adwa

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም.
Le 1er mars 1896



# ኢትዮጵያ ጣልያንን አሸነፈች
# L'Éthiopie gagne l'Italie

☞ አፍሪካ ቅኝ ገዢዎችን አሸነፈች።

L'Afrique a vaincu les colonialistes.

☞ ጥቁር ሕዝቦች ነጮችን አሸነፉ።

Le peuple noir a vaincu le peuple blanc.

☞ በቅኝ ግዛት ሥር ያሉ ሕዝቦች ለነፃነት ተነሱ።

Les peuples colonisés se sont soulevés pour la liberté.

☞ ቅኝ ግዛት ተሸነፈ።

La colonisation a été vaincue.

# ኢትዮጵያ ጣልያንን አሸነፈች ...
# L'Éthiopie gagne l'Italie ...

ብዙ አገሮች የኢዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለማትን ሰንደቅ ዓላማቸው አደረጉ።

De nombreux pays africains, après avoir obtenu leur indépendance de la colonisation, ont adopté les trois couleurs du drapeau éthiopien comme leur drapeau national.



# ጠቃሚ ነጥቦች
# Points importants

በዓድዋ ጦርነት የተሳተፉት መላው ኢትዮጵያውያን ናቸው።

Toute la nation éthiopienne s'est unie pour la bataille d'Adwa.

ፊደላችን፣ ባሕላችን እስከ አሁን የተጠበቀው አባቶቻችን እና እናቶቻችን በዓድዋ ጦርነት ራሳቸውን መሥዋዕት አድርገው ቅኝ ገዢዎችን ስላሸነፉ ነው።

Notre alphabet et notre culture ont été préservés jusqu'à aujourd'hui parce que nos pères et nos mères se sont sacrifiés et ont vaincu les colonialistes lors de la guerre d'Adwa.




ታሪክን መማር አስፈላጊ ነው።

Il est important d'apprendre l'histoire.

አገርን መውደድና ለአገር መልካም ነገር ማድረግ አስፈላጊ ነው።

Il est important d'aimer son pays et de faire du bien à la

# ዋቢ
# Références


https://jpellegrino.com/teaching/scrambleforafrica.html

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣1983 ዓ.ም.

ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1984 ዓ.ም.

Berkeley, G.F.H. 1902. The campaign of Adowa and the rise of Menelik

Jonas, Raymond. 2011, The Battle of Adwa: African Victory in the Age of Empire.

Pakenham, Thomas. The Scramble for Africa, London, Abacus, 1991.

አመሰግናለሁ። Merci.



ጥያቄ? Avez-vous des questions?